የቤተሰብ ውህደት

# የዓለም አቀፍ ጥበቃ የጥገኝነት ሰነድ ላገኙ ስደተኞች

## የቤተሰብ ውህደት ምንድን ነው?

የቤተሰብህን አባላት በሕጋዊና ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ወደ ጣሊያን ለማምጣት የሚያስችል አሰራር ነው።

## የትኞቹን የቤተሰብ አባላት ወደ ጣሊያን ማምጣት ትችላለሁ?

ከሚከተሉት የቤተሰብ አባላት ጋር እንደገና ለመገናኘት ማመልከት ትችላለህ፡-

- **የትዳር ጓደኛ** - (ባል ወይም ሚስት) በሕጋዊ መንገድ  ያልተለያየና ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች ያልሆነ ፣ ወይም በፍትሐ ብሔር የተጋባ (በጣሊያን ወይም በውጭ አገር) ፣ የውጭ ዜጋ የሆነና በጣልያን የማይኖር;
- **ልጆች** - ከዕድሜ በታች የሆኑ ልጆችህ፣ በጉዲፈቻ የተደገፉ፣ የምታሳድጋቸው ልጆች ፣ በሞግዚትነት፣ የምታሳድጋቸው፣ የባለትዳርህ ልጆች ወይም ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ፣ ከትዳር ውጭ ተወልደው ኣንዱ ወላጅ ካለና ለሌላው ወላጅ እንዲያሳድገው ሃላፊነት ከሰጠው;
- **ልጆች** - ከዕድሜ በላይ የሆኑ ባንተ ስር የሚተዳደሩ ልጆችህ  በተገቢ ምክንያቶች አስፈላጊ ፍላጎቶቻቸውን ማቅረብ የማይችሉ ከሆነና ሙሉ በሙሉ የአካል ጉዳተኞች ከሆኑ;
- **ወላጆች** - እስከ  65 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ወላጆች፡ ባንተ ስር የሚተዳደሩ ሆነው ባገራቸው ወይም በሚኖሩበት ኣገር ሌሎች ልጆች ከሌሉዋቸ;
- **ወላጆች** -ከ  65 ዓመት በላይ የሆኑ ጥገኛ ወላጆች ፣ ሌሎች ልጆች ካሏቸው፡ ግን እነሱን መደገፍ የማይችሉና ከባድ የጤና ምክንያቶች እንዳላቸው ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ።

ዕድሜህ ከ 18 ዓመት በታች ከሆነና ብቻህን ከሆንክ ፣ ከወላጆህ ወይም ከሚንከባከቡህ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ተለይተህ በጣሊያን ውስጥ እንደ ስደተኛ የጥገኝነት እውቅና ካገኘህ፡ የወላጆችህ ዕድሜና ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ከወላጆች ህ ጋር እንደገና የመገናኘት መብት አለህ።

## ለቤተሰብ ውህደት ለማመልከት ምን ያስፈልገኛል?

ለቤተሰብ ውህደት ለማመልከት የሚያስፈልጉ፡-

- የመኖሪያ ፈቃዱ፡ ያልወደቀ ወይም በሚታደስበት ሂደት ውስጥ መሆን አለበት ። እንደዚህ ከሆነ ማመላከቻው መኖርያ ፈቃዱ ከመውደቁ በፊት በ 60 ቀናት ውስጥ ማመልከት;
- ፓስፖርት ወይም የጉዞ ሰነድ ( ሰነድ ካለ);
- ዝምድናህን የሚያረጋግጡ ሰነዶች፣ ከዕድሜ በታችና የቤተሰብ ማረጋገጫ ሰነድ (ካለ)።

የዓለም አቀፍ ጥበቃ ሰነድ ባለቤት እንደመሆንህ ፣ ለሌላ የአውሮፓ ህብረት ላልሆኑ የውጭ ዜጎች የቀረበውን የገቢና የመኖሪያ ቤት ብቁነት መስፈርቶችን ማሟላት አይጠበቅብህም።

## የቤተሰብን ውህደት አሰራር እንዴት መጀመር እችላለሁ?

የአሰራር ሂደቱ ሁለት ደረጃዎችን ያካተተ ነው፡ **የኑላ ኦስታን** ጥያቄ በምትገኝበት ግዛት **የስደተኞች ጉዳይ የሚመለከት ጽ/ቤት (ስፖርተሎ ኡኒኮ)** መጠየቅና በውጭ አገር በጣሊያን ኤምባሲ ወይም ቆንስል የቪዛ ጥያቄን መከተል።

**ኑላ ኦስታን** ለመጠየቅ ማድረግ ያለብህ:

- የ **ስፒድ (SPID)** ዲጂታል መሳርያ ማግኘት (በጣልያን ፖስታ ቤት በመሄድ ማግኘት ትችላለህ);
- የ 16.00 ዩሮ የቀረጥ ማህተም መግዛት (ማርካ ዳ ቦሎ);
- **ስፒድ** የሚሰራውን ስራ በማመስገን፡ በዚህ ድረገጽ **www.nullaostalavoro.dlci.interno.it** በመግባት የሚከተለውን ሰነድ በሞምላት የገዛሀውን የቀረጥ ማህተሙን (ማርካ ዳ ቦሎ)ቁጥር መሙላት;

ከዚያ በምትኖርበት ቦታ የሚገኙ **የኢሚግሬሽን ጽ/ቤት (ስፖርተሎ ኡኒኮ)** ይጠሩሃል እናም የሚከተሉትን ሰነዶች ይዘህ መሄድ ያስፈልገሃል:

- ማመልከቻው ስታመለክት ቁጥሩን በማመልከቻው ያካተትከው ማርካ ዳ ቦሎ ኦሪጂናሉ;
- ሌላ የ € 16.00 የቀረጥ ቴምብር በኑላ ኦስታ ላይ የሚለጠፍ;
- የመኖሪያ ፈቃድህና ፎቶ ኮፒ;
- ለሚመጡት የቤተሰብህ አባላት የሰነዶቻቸው ቅጅ (ካለ)።

የቤተሰብህ የዝምድና ሁኔታ የሚያረጋግጥ ሰነድና የመኖርያ ኣድራሻ (ራስህን ጽፈህ ልታዘጋጅ ትችላለህ)።

**ኑላ ኦስታን** አንዴ ካገኘህ በኋላ ቪዛውን ለማግኘት፡ ኦሪጂናሉ ወደ ቤተሰቦችህ በመላክ፡ ወደሚመለከተው የጣልያን ቆንስል ወይም ኤምባሲ እንዲሄዱ ማድረግ፡ እስከዚያው ኤምባሲው በቴሌማቲክ ወይም በመስመር **ከኢሚግረሽን ኦፊሱ (ስፖርተሎ ኡኒኮ)** ይደርሰዋል።

እንዲሁም ከስፖርተሎ ኡኒኮው; የጽሑፍ መልእክት ከነስልክ ቁጥሩ ይላክልሃል፡ በዚህም መሰረት ወደ ጽ/ቤቱ **(ስፖርተሎ ኡኒኮ)** በመሄድ ለቤተሰብህ ቀጠሮ ትይዛለህ። በእርግጥ የቤተሰብህ አባል ጣሊያን ከገባበት ጊዜ አንስቶ ጽ/ቤቱ ለማነጋገርና የመኖሪያ ፈቃድ እንዲሰጥ ለመጠየቅ 8 ቀናት ይኖራቹሃል።

## ምን ያህል ጊዜ አስፈላጊ ነው?

ሁሉንም ነገር በትክክል ካከናወንክና ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ፡ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ 90 ቀናት ውስጥ ኑላን ኦስታውን ታገኛለህ። የኑላ ኦስታ ጥያቄ በሆነ ምክንያት ተቀባይነት ካላገኘ ግን የእሱ መብት እንዳለህ ካመንክ፡ ለመኖሪያው ቦታ ተራው ፍ/ ቤት (ልዩ ክፍል) ይግባኝ ማለት ትችላለህ።

ሕጉ ቪዛው ከተጠየቀ በ 30 ቀናት ውስጥ እንዲሰጥ ይጠይቃል ፣ ግን ጊዜው ሊረዝም ይችላል።

*በጣልያን ካሪታስ፣ ከንሶርስዮ ከሙኒታስና ዩኤንኤችሲአር የተዘጋጀ፡- የበለጠ መረጃ ለማግኘት http://ricongiungimento.it/ ይመልከቱ።*